# እንደ ታዛቢ ፣ እንደ አንባቢ

ታሪኩ አባዳማ ሐምሌ 2004

ግንቦት ወር አጥቢያ ግድም ፍትህ በተሰኘው የአገር ቤት ጋዜጣ ላይ ዋና አዘጋጁ እና ሁዋላ ደግሞ ፕሮፌሰር መስፍን 'በህጋዊ' መንገድ ሰላማዊ ትግል እያራማዱ ስለሚገኙ ድርጅቶች የሰነዘሯቸውን አስተያየቶች ሳነብ የምንገኝበት የትግል እርከን ከምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ የሚፈነጥቅ ተጨማሪ ግንዛቤ አግኝቻለሁ። ምን አዲስ ነገር ነገሩን? የምናውቀውን ፣ በየጓዳው ብለን የሰለቸንን ወይም ፀሐይ የሞቀውን ጋዜጣ ላይ ስላተሙት ካልሆነ በቀር ቁምነገር የለውም የምንል አንጠፋም። እኔ ግን እንደ አንድ ተራ ኢትዮጵያዊ በመጣጥፎቹ በተወሳው ሁተታ 'ንቃተ ህሊናዬ' የጨመረ ቢሆንም ንቃተ ናላዬ ደግሞ ዞር እንዳለ መደበቅ አልሻም።

ይህ ግልፅነት እና ቁጭት የታከለበት ሂስ አዘል አስተያየት አገር ቤት መፈናፈኛ አጥተው በሚውተረተሩ ተቀዋሚ ድርጅቶች እና መሪዎች ዙርያ ተንሰራፍቷል የተባለውን ድክመት ከመጠቆም አልፎ ምን ሊደረግ ይገባል የሚል ምክር ጭምር ለመለገስ ሙከራ የተደረገበት ነው። ታዛቢዎቹ እንዳብራሩት ሁኔታው እንዲህ ከቀጠለ ደርጅታዊ ትግሉ ሳያምርበት ሀያ ዓመት እንዳለፈ ሁሉ ብሶበት እንደሚቀጥል ከወዲሁ ይጠቁማል። እርግጥ ነው ጉዳዩ አዲስ ላይሆን ይችላል ሆኖም ይፋ ርዕስ ሆኖ በነፃ ጋዜጣ ሲተችበት የመጀመሪያው ነው።

መጣጥፉ የቀሰቀሰብኝን ራስ ምታት በቴዲ አፍሮ ሙዚቃ 'ጥቁር ሰው' አረጋግቼ እኔም በበኩሌ ያለኝን አስተያየት ለማከል እና በነካ እጅ አገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን እዚህ ፈረንጅ አገር ስላለው የትግል እና ድርጅቶች ጉዳይ ጭምር እንደገና አንድ ነገር ለማለት ወሰንኩ።

ሶስት ወር ፈጀብኝሳ!! እንቅልፍ አበዛሁ እንዴ?

'ኢጆሌ በያኮ ጀጀባዳ መሌ
ጀዴቶ ካኤ አገሬ ጎበሌ
ዱብት ኢንዴምኑ አልከን ታኤ ጉያ
ዲናፍ ኢላኑ ኢትዮጵያ። ጄዴ'

ይለዋል ቴዲ በኦሮሚፋ(ጥቁር ሰው)

ውርስ ትርጉም - 'የሁዋልዮሽ እየሄድን ኢትዮጵያን ለጠላት እራት አናድርጋት' ነው መልዕክቱ።

እንደወትሮው ሁሉ ጆሮ ያለው ይስማ ብሎ የቀመረው ስንኝ ነው!!

እኔን ካንቀላፋሁበት ቀስቅሶኛል።

የሆነው ሆነና ከአገር ሆነ ከውጭ የሚሰነዘሩ አስተያየቶችን ግምት ሰጥቶ መመርመር እና ተገቢ እርምት መውሰድ በቅድሚያ የፖለቲካ መሪዎች ብሎም የሁሉም ዜጋ ሀላፊነት እንደሆነ የሚጠፋው ሰው የለም። ሰምቶ እንዳልሰማ አይቶ እንዳላየ ወይንም ለሚሰነዘሩ ገንቢ አስተያየቶች ወቅታዊ እርምጃ አለመውሰድ እና ራስን አለመፈተሽ ዞሮ ዞሮ ውጤቱ አሁን እንደምናየው ድክመቱ በጠባብ የድርጅት 'ፍቅር' ዙርያ ተወስኖ በመግለጫ እና በወግ ጥረታ ብቻ ተጀቡኖ ፣ ትግሉ እንደ ከርሞ በተያያዘው የቁልቁለት ሩጫ ይቀጥላል።

ፍትህ ጋዜጣ ላይ የታተመውን አስተያየት ስንቶቻችን እንዳነበብነው ወይም ምን ያህል መልዕክቱን እንደመረመርነው መገመት ባልችልም እውነቱ ግን ነፃይቱን ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ እውን ለማድረግ አገር ውስጥም ሆነ ውጭ እየተደረገ ያለው ትግል ወያኔ እያጎለበተ ከሄደው አፈና እና ማን አለብኝነት ጋር ሲነፃፀር የት እየለሌ ነው ያስብላል።

እዚህ መጣጥፍ ላይ እንደ ፍትህ ጋዜጣ ሁሉ የድርጅቶችን ወይንም የግለሰቦችን ስም አንስቼ ለመተቸት አልሞክርም። ይህን የማላደርገው ለትግሉ መሽመድመድ ተጠያቂ እገሌና እገሌ ናቸው ወደሚል መደምደሚያ አንሸራትቼ ሃያ አንድ ዓመታት ተንጣሎ ሲሰለቅጠን ከቆየው ማጥ ውስጥ እንዳልከታችሁ ስጋት ስላለኝ ሲሆን ከማጡ ጎትተው የሚያወጡንም እነዚያ የምንጠቃቀሳቸው ግለሰቦች ወይንም ድርጅቶች ብቻ ናቸው የሚል እንደምታ ህሊናችሁ ውስጥ ማሳደር ትክክል እንደማይሆን በማመን ጭምር ነው።

አጠር ባለ አገላለፅ ፍትህ ጋዜጣ ላይ ያነበብኩት ቁምነገር እና እኔም የምስማማበት ጉዳይ አንድ ፓርቲ ፈላጭ ቆራጭ ብሎም ከአንድ ጎጥ የተነሱ ወራሪዎች (gangs ወሮ በሎች?) ሁሉን አድራጊ በሆኑባት አገር ዘንድሮም እንደ አምና ካቻምናው በደላችን እየገዘፈ ፣ ብሶታችን እየገነፈለ ቁጣችን እያስተጋባ ቢሆንም ፣

ገዝፎ የሚታየውን የህዝብ ብሶት እና ምሬት በወጉ አማክሎ ለዘላቂ ሰላምና ሰብአዊ ክብር የሚያበቃ የምንመካበት የምንተማመንበት አንዳች የረባ መሳሪያ እጃችን ላይ የለም። በወጉ አልተደራጀንም ፣ ተነጋግረን ለመደማመጥ አልበቃንም ፣ አንተ ትብስ ተባብለን ትግሉን ወደፊት ማራመድ አልቻልንም።

እንበለ-ህግ በዜጎች ላይ የሚፈፀመው ሰቆቃ የሰው ህሊና ሊቀበለው ከሚችለው በላይ ተባብሶ ቀጥሏል። በየወረዳው እና ቀበሌው የዘለቀው ግፍ ዜጎች ካፅመ ርስታቸው እየተፈናቀሉ ፣ አምልኮ ገዳማት ሳይቀሩ ህልውናቸው ተናግቶ የመነኩሳት ዋይታና ለቅሶ እያስተጋባ ነው። የግፈኛው መንግስት ተራ እና ተርታ የጥቃት ስልቶች መላ አገሪቱን አጥለቅልቀዋል። ነፃነት ተርበናል ፣ ተጠምተናል።

በከፋፍለህ አስገብር መርህ ላይ ተጠናክሮ የቀጠለው ወያኔ 'የብሔር ብሔረሰብ ነፃ አውጭ ነኝ' ብሎ በአምሳሉ መቶ እና መቶ ተለጣፊ ጎጠኛ ድርጅቶች በፈለፈለባት አገር ብሔረሰቦቻችን ማንነታቸው ሳይናጋ ለዘመናት ከኖሩባቸው ሩቅ ቄየዎች ሳይቀር እየመነጠረ በማጥፋት ላይ ይገኛል።

ወገኖቻችን ባህላዊ እና መንፈሳዊ ትስስር ፈጥረው ከኖሩባቸው ተራሮች ፣ ሸንተረሮች ፣ ደኖች እና ወንዞች እየተፈናቀሉ ብሔረሰብነታቸው ይቅርና ሰብአዊ ፍጡር መሆናቸው ህልውናቸው እየደበዘዘ ነው። ያንዲት አገር ዜጋ መሆናቸው ተሸሯል ፣ ማንነታቸው ከስር መሰረቱ እየፈራረሰ ነው። የተባበሩት መንግስታት ይህን በልማት ስም ዜጎችን ከጥንታዊ ቀያቸው ማሳደድ አውግዞ ያወጣውን መግለጫ ሰሞኑን አንብበናል።

የብሔረሰቦቻችን መንደሮች በስለታም ምላጭ የሽቦ አጥር ተከልለው በህንድ እና አረብ ቡልዶዘር ይታመሱ ዘንድ የብሔረሰቦች 'ነፃ አውጭ' ነኝ የሚለው ወያኔ በይኖባቸዋል።

ባዕዳን ቱጃሮች ያሻቸውን አምርተው በፈቀዱት አለም ገበያ ቸብችበው ትርፍ እንዲያገበሰብሱ በትግራይ ነፃ አውጭ ድርጅት ህወሃት ያልተሸራረፈ 'ነፃነት' ተጎናፅፋዋል። የህንድ ፣ ቻይና እና አረብ ቱጃሮች ለም በሆነው የኢትዮጵያ ክልል ምን ያህል ስፋት ያለው መሬት እንደሚሹ እንኳ የሚወስኑት ራሳቸው ናቸው።

አገር በቀል አልሚዎች ሰፋፊ መሬት ያዛችሁ ተብሎ 'በአድህሪነት' በአብዮት ጥይት ያለቁባት አገር ያንኑ ለም ድንግል መሬቷን እጥፍ በእጥፍ ለቀማኛ ባዕዳን አሳልፋ ስትሰጥ በኛ ዕድሜ አያየን ነው።

የትግራይ ወጣቶች ያለቁት ድንግል መሬታችንን ለቻይና እና አረብ ቱጃር ለማስታቀፍ ነበር? በነፃነት ይኖሩ የነበሩ ዜጎች ከቄያቸው ተፈናቅለው ደብዛቸው እንዲጠፋ ነበር?

የትግራይ ነፃ አውጭ ሙታን መልስ ባይሰጡንም እውነቱ ግን ይኸው ነው።

The Guardian የተሰኘው እንግሊዝ ጋዜጣ Karuturi Global የተባለው የህንድ ኩባንያ ኢትዮጵያ ውስጥ እያካሄደ ስላለው የዜጎች መፈናቀል ጉዳይ በቅርቡ ሲዘግብ Locals move out as international contractors seize opportunities offered by government to lease farmland at knockdown rates ብሏል።

በገዛ አገር የኑሮ ውድነት እና የህይወት ዋስታና ማጣት ከሰብአዊ መብት መዋረድ ጋር ተደማምረው መላውን ዜጋ ከዳር እስከ ዳር አስመርረውታል። ባለፉት ሁለት ሳምንታት ብቻ በምስራቅ አፍሪቃ አካባቢ አገራቸውን ጥለው የተሰደዱ ኢትዮጵያውያን በኮንቴይነር ታጭቀው ሌሎች ደግሞ በትንሽ ጀልባ ተጨናንቀው ሲሸሹ ለከፋ የሞት አደጋ መጋለጣቸውን ሰምተናል። ይሁንና የኢትዮጵያውያን ስደተኞች እልቂት እየተለመደ በመምጣቱ ለዓለም ህዝብ ዜና መሆኑ ቀርቷል። አገራችንን የሚነካ ማናቸውም ወሬ "anything could happen in Ethiopia" በሚል መንፈስ ተውጦ ስለመገኘቱ ማረጋገጫ ከፈለጋችሁ በየትኛውም አለም ክፍል ጎዳና ላይ የምታገኙትን ሰው አቁሞ መጠየቅ ብቻ ነው።

'በኢትዮጵያ ሰላማዊ ሰልፈኞች በፖሊስ ጥይት አለቁ ፣ በምግብ እጦት ጠኔ የሚረግፈው ህዝብ ይህን ያህል ሚሊየን ነው ፣ ጋዜጠኞች ወህኒ ገቡ ፣ የተቃዋሚ ድርጅት መሪዎች ተገደሉ፣ ታሰሩ ፣ ተሰደዱ ፣ ስደት ጉዞ ላይ የነበሩ ኢትዮጵያውያን ውሀ በላቸው ፣ አረብ አገር ስራ ፍለጋ የወጡ ዜጎች ግፍ ተፈፀመባቸው ፣ አገሪቱ ሙስና ተንሰራፋባት ፣ ጠ/ምኒስትሩ ሀያ አንድ ዓመታት ቀጥቅጦ ገዛ ፣ ሚስቱ ህገወጥ ነጋዴ መሆኗ ተረጋገጠ… ይህንና ይህን የመሳሰሉ ጉዳዮች ሲነገሩ መስማት ዜና መሆኑ ቀርቷል።

አገዛዙ በዚህ ሁሉ የብሶት እና ምሬት ክምችት ውስጥ እንዴት መቀጠል ቻለ የሚለው ጥያቄ ግን ሁሉንም ወገን የሚያስደምም ጉዳይ መሆኑ ግልፅ ነው። ፍትህ ጋዜጣ ላይ የተነበበው መጣጥፍ የሚያስተጋባው ኢትዮጵያውያን ሰብአዊ መብታቸው ሲረገጥ ፣ ህልውናቸው ሲናጋ ፣ ለስደት እና ረሀብ ሲጋለጡ እንዴት

አንድ ሆነን ተባብረን መላ ማፈላለግ ተሳነን የሚለውን እንቆቅልሽ ነው። አስተያየት ሰጭዎቹ ጥያቄው የጠንካራ መሪ ድርጅት አለመኖር ጉዳይ መሆኑን ጭምር ግልፅ በሆነ ቃል አስምረውበታል።

ወያኔ በበኩሉ በአገርም ሆነ ውጭ የሚንቀሳቀሱ ተቀዋሚ ወገኖች ተባብረው ለመስራት የማይችሉ መሆኑን እንዳረጋገጠ ሁሉ አገዛዙን የሚያሰጋ እንደሌለ በማመን እንደተኮፈሰ ነው። ማን አለብኝ ብሎ ከጥፋት ለመቆጠብ አለመፈለጉ ሌላው ወገን ምን ያመጣል በሚል ካደረበት ንቀት ጭምር የተነሳ መሆኑን በማያሻማ ሁኔታ መናገር ይቻላል። ዛሬም እንደ ሀያ ዓመት በፊቱ እንደተናቅን ፣ እንደተዋረድን ነን።

በውጭ ያሉ ተቀዋሚ ድርጅቶች ውሎ እና አዳር ምን እንደሚመስል ለመፈተሽ ሩቅ መጓዝ አያስፈልግም ፤ ዛሬ ሁሉም ነገር በድረ-ገፅ ፤ በፓልቶክ ፤ ቴሌ-ኮንፈረንስ… ላይ እየቀረበ ትግሉ ስልቱ መቼ እና ምን ማድረግ እንደተፈለገ ሁሉ እቅድ ይዘረጋል። በትግል እና በምኞት ፣ በመስዋዕትነት እና በችሮት መካከል ያለው ልዩነት እንደተምታታብን ሁሉ ምን እንደጨበጥን እና የት እንዳለን ለመረዳት ተስኖናል።

ድረ-ገፆችን አድምቀው ቀልባችንን ሲቆጣጠሩት የምናያቸው ስዕሎች የወሳኙ ትግል ገፅታዎች መሆናቸው ቀርቶ በትግሉ ውስጥ ከአጋርነት ያልዘለለ ሚና ሊኖራቸው የሚችሉ ሰዎችን ነው። ማነው ትግሉን ሊመራው የሚችለው? በሙያቸው አገልግሎት በማበርከት ላይ ያሉ ሰዎች ትግሉ የወለዳቸው ቆራጥ ባለሙያዎች ናቸው አዎን የሚያኮሩ ናቸው ግን ትግሉ እነሱ ከተካኑበት ሙያ በላይ ውስብስብ እና የተለየ ባህሪ ያለው መሆኑን መገንዘብ ይገባል። አለበለዚያ እነሱን ማሞጋገስና 'በናንተው መጀን' ማለቱ ስር እየሰደደ ከሄደ የትግሉ ሂደት እየመከነ መሄዱ አይቀርም።

በዚህ ረገድ ዞትር የምንዳስሳቸው ድረ-ገፆች ብቻ ሳይሆኑ ወያኔ ራሱ ሆነ ብሎ ትግሉን ለመምራት አንዳችም ዝግጁነት ወይንም ብቃት በሌላቸው ሰዎች ላይ እንድናተኩር ስማቸውን አንዴ 'አሸባሪ' ሌላ ግዜ 'ከሀዲ' እያለ እነሱን እንደሚፈራቸው እና እንደሚያሰጉት ሊያሳየን ይሞክራል። ኢትዮጵያውያን ሊያነጣጥሩበት እና ሀይላቸውን ፣ ትኩረታቸውን ሊያጎለብቱ የሚበቁበት ሁኔታ እንዳይመቻች በተቀነባበረ የወያኔ ስልት ሲሰራበት የቆየ ማደናገሪያ መሆኑ ለስንቶቻችን ግልፅ ሆኖ እንደሚታየን አላውቅም።

ሁሉም እንደ ችሎታው ለትግሉ የሚያበረክተው አስተዋፅዖ ታላቅ ዋጋ እንዳለው መካድ ባይቻልም እንደ ባለ ሙያ ፣ እንደ ባለ ተስጥዖ ልንጫወት ከምንችለው ውሱን ሚና በላይ የተጋነነ ድርሻ እንደምናበረክት አድርገን እኛም እንዲሰማን ሌላው የዋህ ዜጋም አልሆነ ቦታ ላይ ትኩረቱ እንዲሳብ የሚደረገው አዝማሚያ ረገብ ሊል ይገባል። ትርፉ 'ዶሮን ሲያታልሏት…' ሆነን በጠላት ጓዳ ጭምር መሳለቂያ መሆን ነው።

ወደ ድርጅቶች ጉዳይ እንመለስ - ኢትዮጵያ በጠላት እጅ ወድቃ በቆየችባቸው ባለፉት ሀያ አንድ ዓመታት ከፖለቲካ ድርጅቶች ምን ይጠበቅ ነበር? ማከናወን ይገባቸዋል ተብሎ ከሚጠበቅባቸው ውስጥ ምን ፍሬ ያለው ነገር አከናወኑ? ምንስ ሳይከናወን ቀረ? ማድረግ የማይገባቸውን ምን አደረጉ? ሲያደርጉ ከቆዩት በጎ ነገር ውስጥስ ሊጠቀስ የሚገባው የትኛው ነው? በዚህ ሁሉ ሂደት ውስጥ የግለሰቦች በተለይም የድርጅት መሪዎች ሚና ምን ነበር? ትግሉ እውነትም ኢትዮጵያን ነፃ ማውጣት ከሆነ ያንን የነፃነት ትግል ለማካሄድ ምን አይነት ድርጅታዊ ፣ መንፈሳዊ እና አካላዊ ጥንካሬ ይጠይቃል? ያንንስ ለማሟላት ምን ሲደረግ ቆየ? ዛሬስ ከትናንቱ ትምህርት መቅሰም ተችሏል?

ጥያቄ በጥያቄ - በጣም ብዙ አጣዳፊ መልስ የሚሹ ጥያቄዎች።

አረመኔው ጎጠኛ ጠ/ሚኒስትር የአልጋ ቁራኛ መሆኑ በተነገረበት በዚህ ሰሞን አገራችን ውስጥ ይፈጠራል ተብሎ በሚጠበቀው የስልጣን ክፍተት ዙርያ ምን ማድረግ እንደሚገባን በሰከነ እና በተማከለ መልኩ ሊነግረን ሊመራን የሚችል ድርጅት አለመኖሩ ተንሰራፍቶ ለቆየው ድክመት በቂ ማረጋገጫ ነው። የመለስን በጠና መታመም እንደ ሌሎች ዜና አውታሮች ሁሉ ተቀዋሚ ድርጅቶቻችንም ሀተታ ፣ ግምት ፣ ግምገማ እያስነበቡን ነው። ሳይሞት አይቀርም ፣ ወደ ስራው አይምለስም፣ ሽባ አካለ ጎደሎ ሆኗል… ከሚለው ጀምሮ ማን ይተካው ይሆን? የሚሉ መላ ምቶች እየተሰነዘሩ ነው - መልካም።

ግን ምን ይፈጠር ይሆን ከሚል የዘለለ በዚህ አጋጣሚ ጠላት ሰፈር የተነሳውን መደናገር ታምቆ ለቆየው ህዝባዊ ብሶት መቀጣጠል እንዲጠቅም ለማድረግ አንዳችም እንቅስቃሴ ሲደረግ አልተሰማም።

መለስ ሞተ አልሞተ የትግሉን መሰረታዊ ጥያቄ የሚለውጠው የለም።

መጨረሻ ገፅ ላይ ባነሳሁዋቸው ጥያቄዎች ዙርያ የምለው ብዙ አለ - በሚቀጥለው ፅሁፌ እምለስበታለሁ። ከቻላችሁ ተከታትላችሁ አንብቡት።